የአዲሱ ፓርቲ ፕሮግራም

ረቂቅ ሠነድ ለውይይት የሚቀርብ



ሚያዚያ 2011
ረቂቅ ሠነድ

ማውጫ

መግቢያ 2

1. የፖለቲካፕሮግራም 4

1.1. የፖለቲካ ሥርዓቱ አደረጃጀት 4

1.2. አጠቃላይ የመንግስት አደረጃጀት 4

1.3. የፌዴራል መንግስት አደረጃጀት 5

1.4. ሰብአዊና ዴሞክራስያዊ መብቶች 5

1.5. የሃገር መከላከያ ሰራዊት፣ ፖሊስና ድህንነትን 6

2. የኢኮኖሚ ፕሮግራም 6

2.1. መርዕዎች 6

2.2. የግብርና፣ አርብቶ አደር ዓሣ ልማት 7

2.3. ኢንዱስትሪ/የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ 7

2.4. የአገልግሎት 7

2.5. የተፈጥሮ ሀብትና መሬት 8

2.6. የከተማ ልማት 8

2.8. ፋይናንስና ባንክ የአገልግሎትን 8

3. የማሕበራዊ ፕሮግራም 9

3.1. ድህነት ማጥፋት 9

3.2. የሰው ሀይል ፍልሰትና ስደት 9

3.3. ትመህርት 9

3.4. የጤና አገልግሎት 9

3.5. ማህበራዊ ዋስትና 10

3.6. ሴቶች 10

3.7. ወጣቶች 10

3.8. አካል ጉዳተኞች 10

3.9. አረጋውያንና ወላጃቸውን ያጡ ህጻናት 10

3.10. ስነ ሕዝብን 10

3.11. ቅርሶችና ብሄራዊ ፓርኮች 11

3.12. ሰፖርት፣ ኪነጥበብ፣ አርት ሳይንስና ቴክኖሎጂ 11

4. የውጭ ግንኙነትና የአከባቢ ሰላም ፕሮግራም 11

5. በውጭ የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን እና ኢትዮጵያዊያን ፕሮግራም 12

DRAFT

መግቢያ

አገራችን ኢትዮጵያ ረዥም የመንግስትነት ታሪክ ያላት አገር ብትሆንም፣ ይሄ ባለረጅም መዋዕልነቷ ዜጎች በነፃነትና በእኩልነት የሚኖሩባት፣ መሪዎቻቸውንም በሰላማዊ መንገድ ወደ ስልጣን የሚያወጡበትና የሚያወርዱበት ስርዓት ሊያጎናፅፋት አልቻለም፡፡ ገዢዎች በሆነ የታሪክ አጋጣሚ በኃይል ሥልጣን ይይዛሉ፤ በመጡበት መንገድ በኃይል መልሰው ቦታቸውን ያጣሉ፤ ይሄ ሁኔታ ዜጎቿን ለጦርነት፣ ለመከራና ለድህነት የዳረገ፣ አገሪቷንም በዘመናት የዳበረና የሰለጠና መንግስታዊ ስርዓት እንዳይኖራት አድርጓታል። በየጊዜው በተሞከሩት ለውጦች፣ በተለይ ደግሞ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ውስጥ ይህ ታሪክ ይለወጣል የሚል ተስፋ የነበረን ቢሆንም አሁንም ሀገራችን ከአንድ ፓርቲ አንባገነን ስርዓት ልትላቀቅ ያልቻለች ቢሆንም፤ በቅርቡ ለለውጥ ፍላጎት መኖሩን የሚያሳዩ ምልክቶች መኖራቸው አበረታች ጅምር ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡

በነበረው ሥርዓት በሚከተለው የፖለቲካ አካሄድ በዚህም መነሻ የሚመነጩት የፖለቲካና ማህበራዊ ፖሊሲዎች ምክንያት አገራችን አሁን የምትገኝበት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ችግሮች ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ ሲሆን፤ ካለንበት ፈርጀ ብዙ ችግሮች የተነሳም በዓለም ላይ ካሉት እጅግ በጣም ድሀ አገሮች ውስጥ የምትመደብ፣ ዜጎቿን መቀለብ የማትችል፤ በየጊዜው በሚፈጠረው ድርቅ ምክንያት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች የሚራቡባት፤ ወጣቶቿ ለስደትና ለባዕዳን ግርድና የተዳረጉባት፤ ከፊቷ ብዙ አደጋዎች የተደቀኑባት አገር ሆናለች፡፡ ይህ ሁኔታ በረጅምና በአጭር በተተለመ እቅድ ለመቀየር ካልተቻለ አሁን ካለችበት ሁኔታም የባሰ ነገር እንደሚጠብቃት መገንዘብ ነብይ መሆን የሚጠይቅ ነገር አይደለም፡፡ በአጠቃላይ ይህ በእያንዳንዱ ዜጋ ላይ ቁጭት ሊፈጥር የሚችል እና የሚያሳፍር የአገራችን ገፅታ በዘላቂነት መለወጥ ብቻ ሳይሆን፤ ታሪክ ሆኖ እንዲቀር ለማድረግ ዜጎች ሁሉ በጋራ መነሳት እና መረባረብ ይጠይቀናል፡፡ በመሆኑም ለዚህ የሚሆን ስርዓት መዘርጋት የግድ የሚለን ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡

ኢትዮጵያ አገራችን ልዩ ልዩ ማንነቶችና እምነቶች ያሉባት አገር መሆኗ የሚታወቅ ነው፡፡ የአገራችን ብዝሃነት የሚገለፀው በቋንቋ ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰብ ጭምር መሆኑን እነዚህ የተለያዩ ማንነቶች በሚያቅፍና በሚያስተናግድ መልኩ በጋራ እሴቶች ላይ የተመሰረተ አብሮነትን የሚያፀና በዜግነት መብት ላይ የሚመሰረት ህገ መንግስታዊ ስርዓት ማምጣት አስፈላጊ መሆኑን በማመን ፓርቲያችን በዜግነት ላይ የተመሰረተ የሃሳብ መቀራረብ ያላቸው አባላትን ያቀፈ የፖለቲካ ሰብስብ ሆኖ ይመሰረታል፡
፡

ፓርቲያችን እንደ አንድ ሀገራዊ ፓርቲ በሀገራችን ውስጥ የዜጎችን ነፃነት የሚያከብርና የሚስከብር መንግሰት ለመመስረት የፖለቲካ አማራጮችን በማቅረብ፤ የመድበለ ፓርቲ ስርዓት እንዲያብብ አማራጭ የፖለቲካ ሀይል ሆኖ ይቀርባል፡፡ ፓርቲያችን የነበረውን ኢፍትሓዊነት ለማረም በሚያስችል መልኩ ማህበራዊ ፍትህ ማስፈንን መሰረት ያደረገ የፖለቲካ ዘይቤ የሚከተል ቢሆንም፣ ይህ ርዕዮተ ዓለም ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታና ነባር እውቀቶች ጋር በማዋሃድ የሚተገበር ይሆናል፡፡ የሚቀርፃቻው ፖሊሲዎች ሁሉ የብዙሃኑን ተጠቃሚነት በቀጥታ የሚያረጋግጡ ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ሀገራችን የሚፈጠር ሰላማዊ የስልጣን ሽግግርም ሆነ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ በአፍሪካ ቀንድ ብሎም ለአፍሪካ በተምሣሌትነት የሚታይ መሆኑን በመረዳትና ይህንን ማድረግ የሚችል ድርጅታዊ አቅም መፍጠር ወሳኝ መሆኑን በመረዳት፤ ፓርቲያችን ጠንካራ ድርጅት ለመፍጠር የሚቻለውን ሁሉ ያድርጋል፡፡ ይህን ለማሳካት የሚቻለው ደግሞ ዜጎች በነፃነት ፓርቲያችንን ሲቀላቀሉ መሆኑን በማመን ይህን ረቂቅ ፕሮግራም በማንበብ ፓርቲያችንን እንዲቀላቀሉ ይጋብዛል፡፡

ይህ ፕሮግራም አምስት ከፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የፓርቲውን የፖለቲካ ፕሮግራም በተለይም የፖለቲካና የፌዴራል ሥርዓቱን አደረጃጀት፣ የሰብዓዊና ዴሞክረሲያዊ መብቶችን እንዲሁም የመከላከያ ደህንነት ፖሊስ በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ የፓርቲውን አቅጣጫ ያመላክታል።

በሁለተኛና ሶስተኛ ክፍል ከማህበራዊ ፍትሕ ህግቤን መነሻ ያደረጉ የኤኮኖሚና ማህበራዊ አቅጣጫዎች የተጠቆሙ ሲሆን በመጨረሻም በአራተኛና አምስተኛ ክፍል አገራችን በውጭ ግንኙነት እንዲሁም በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ጋር ፓርቲያችን የሚኖረውን ምልከታ ያሰቀመጥል።

DRAFT

1. የፖለቲካፕሮግራም

የፓርቲያችን የፖለቲካ ፕሮግራም በወሳኝ መልኩ ያልተማከለ አስተዳደር (ፌዴራላዊ) ሥርዓትን መከተሉን ምርጫው ያደረገ ሲሆን፣ በሕዝብ ቀጥታ ምርጫ የሚመረጥ ፕሬዝዳንታዊ ሥርዓት እንዲመሰረት አበክሮ ይሰራል፡፡ ፓርቲያችን የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት በማረጋገጥ፤ ዜጎች ከማህበራዊ ፍትህ እሳቢ የሚመነጩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች የሚከተል ፕሮግራም ከሚገኝ ትሩፋት ተጠቃሚ ይሆናሉ ብሎ ያምናል፡፡ ፓርቲያችን ሕገ መንግሥት ማሻሻያ በሥርዓት በማድረግ ዜጎች ተሳትፎ ያደረጉበት መንግሥትን ተጠያቂነት እንዲኖር በትጋት ይሰራል፡፡ ዝርዝር የፖለቲካ ምልከታችን ከዚህ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1.1. የፖለቲካ ሥርዓቱ አደረጃጀት

1.1.1. ፓርቲያችን የሕገ መንግሥት ማሻሻያ መደረግ አለበት ብሎ ያምናል፡፡ ሕገ መንግስቱ የግለሰብ መብትን የመብቶች ሁሉ የማእዘን ድንጋይ አድርጎ እንዲወስደው፣ የቡድንና የወል መብቶች ከግለሰብ መብቶች የሚመነጩ መሆናቸውን የሚቀበል፣በዘር ወይም በእምነት ላይ ያልተመሰረተ፣ ያልተማከለ ፌዴራላዊ አስተዳደር እንዲኖር ይሰራል፣

1.1.2. የፖለቲካ ስልጣን ምንጭ ከህዝብ ይሁንታ የሚገኝ መሆኑን በማመን በነፃ ፍትሓዊ ምርጫዎች ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ አማራጮቹን ለህዝብ ያቀርባል፤ ይህም የሕዝብ የሉዓላዊነት መገለጫ አንደሆነ እና ሥልጣን በሕዝብ ይሁንታ የሚገኝ መሆኑን ማረጋገጫ አድርጎ ይወስደዋል፡፡ የትግል ስልቱም ሰላማዊ ትግል ይሆናል፡፡

1.1.3. ማንኛውም የፖለቲካ ጥያቄዎች በውይይት እና በዴሞክራሲያዊ ስርኣት እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች ወድ ህዝበ ውሣኔ እንዲሄዱ ስርዓት በማበጀት የህዝብ ውሣኔ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

1.1.4. የፓርቲያችን የፖለቲካ ፕሮግራም በማንኛውም ሁኔታ የዜጎችን የኤኮኖሚ ነፃነት፣ ማህበራዊ ፍትህ እንዲሁም የመኖሪያ ምድራችንን ከባቢ ሊጎዳ በሚችል መልኩ አይቀረፅም፡፡

1.1.5. ዜጎች ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎችንም መብቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር በጋራ የመደራጀት፣ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብታቸውን ይከበራል፣

1.1.6. የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ሊገሰስ የማይችልና የማይገሰስ መሆኑን፤ በኢትዮጵያ ሉአላዊ ግዛት ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም የተፈጥሮ ሃብት የሃገሪቱ ዜጎች ሁሉ የጋራ ሃብት መሆኑን ፓርቲያችን ያምናል፣

1.1.7. ዜጎች በመላው ሃገሪቱ ያለምንም ገደብ መንቀሳቀስ መስራትና መኖር፣ ሃብት ማካበት፣ ባካባቢያቸውም ሆነ በሃገሪቱ ፖለቲካ ያለምንም ገደብ መሳተፍ የሚችሉበትን ያልተሸራረፉ መብቶች ያስከበረ፣

1.1.8. የዜጎችን ህይወት ነጻነትና ንብረት መከላከል የሃገሪቱ መንግስት ተቀዳሚና ፍጹማዊ ግዴታ መሆኑን ያምናል።

1.2. አጠቃላይ የመንግስት አደረጃጀት

1.2.1. የመንግስት አደረጃጀት ፌዴራላዊ ይሆናል፡፡ የፌዴራል መንግስትና ክልላዊ መንግስታት ይኖራሉ፡፡ የክልላዊ መንግስት አወቃቀር በሚከተሉት መርሆዎች የተመሰረተ ይሆናል፤

1.2.1.1. መልከአ ምድራዊ አቀማመጥን፣ የሕዝብ አሰፋፈር ለአጠቃላይ አስተዳደራዊና ለልማት ሥራዎች አመቺነትን፤

1.2.1.2. ቋንቋ፤ ባህልና ታሪክን፤

1.2.1.3. የሃብት ስብጥርና ፍትሃዊነት

1.2.1.4. ለብሔራዊ መግባባት አመቺ ሁኔታ መፍጠርን፤ መሠረት ባደረገ ሁኔታ ይሆናል፡፡

1.2.2. ፌዴራላዊ አወቃቀሩ አንዴ ተሰርቶ የሚያበቃለት ሳይሆን የተቀመጡትን መርሆዎችን ጠብቆ በህዝብ ውሣኔ ከኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገታችን ጋራ በመግባባት መንፈስ እየዳበረ የሚሄድ ይሆናል፡፡

1.2.3. የፌዴራል መንግሥቱና እና የክልል የመንግስት ባለሥልጣናት በሕግ የተወሰነ የየራሳቸው የሥልጣን ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ አንዱ በሌላው የውስጥ ጉዳይ እንዳይገባ ይደረጋል፡፡ የየራሳቸው ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈፃሚ እና ሕግ ተርጓሚ ይኖራቸዋል፡፡

DRAFT

1.2.4. አማርኛ የፌዴራል መንግስቱ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል፡፡ እንዲሁም በሕዝብ ውሳኔ ሲፀድቅ ከአማርኛ ሌላ በተጨማሪ ሌሎች ቋንቋዎች የፌደራሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

1.2.5. የክልል መንግስታት የሥራ ቋንቋ የክልሉ ሕዝብ በሚያደርገው ሕዝበ ውሳኔ መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡ የክልል መንግሰታት የዜጎችን በፌዴራል ስርዓት ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ የፌዴራሉን የሥራ ቋንቋ በትምህርት ሥርዓት ውስጥ እንዲካተት ማድረግ ይኖርበታል ብሎ ያምናል፡፡

1.3. የፌዴራል መንግስት አደረጃጀት

የፌዴራል መንግስቱ በሕገ-መንግሰቱ መሰረት ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡ ***በህዝበ ውሳኔ በሚደረግ የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ*** ስርዓት መሰረት አድርጎ የሚከተሉት የፌዴራል ስርዓቶች እንዲዘረጉ ይደረጋል፤

1.3.1.1. በዜጎች ቀጥተኛ ምርጫ በሚመረጠው ፕሬዚደንት ስር የሚቋቋመው የህግ አስፈጻሚው አካልና ህግ በሚያወጡት ሁለት ምክር ቤቶችና ህግ በሚተረጉመው ሶስተኛው አካል መሃል ግልጽነት ያለው ህገመንግስታዊ የስልጣን ክፍፍል እንዲኖር፣ አንዱ በሌላው ስልጣን ጣልቃ እንዳይገባ ማድረግ፣

1.3.1.2. ሕግ አውጪው አካል ሁለት ከፍሎች (የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት) የሚኖሩት ሲሆን ሁለቱም ሕግ የማውጣት ስልጣን ያላቸው እና በሕዝብ የተመረጡ ይሆናሉ፡፡ የፌዴራሽን ምክር ቤቱ አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ብሔረሰቦች ውክልና ከመስጠት በዘለለ አስፈላጊው ድጋፍ እንዲያገኙ ህጎችን የማውጣትና አፈፃፀማቸውን የመከታተል ሃላፊነት ይኖርበታል፡፡

1.3.1.3. ሕገ መንግስቱን የመተርጎም ሥልጣን ሕገ መንግስትን ለመተርጎም ስልጣን ለተሰጠው ሕገ መንግስታዊ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡ ምክርቤቶች ሕግን ማውጣት እንጂ ሕገ-መንግስትን ወይም ሌሎች ሕጎችን የመተርጎም ሥልጣን አይኖራቸውም፡፡

1.3.1.4. የመንግስትን ስራ አስፈጻሚ አካላትን እንዲመራ፣ ዜጎች በአንድ ሰው አንድ ድምጽ መርህ የሚመርጡት የሃገር መሪ እንዲኖር የሚያደርግ ፕሬዚደንታዊ የአስተዳደር ስርአት ይሆናል፣ ፕሬዝዳንቱ የሚመረጠው ለአምስት ዓመት ሆኖ በተከታታይ ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፡፡

1.3.1.5. የአገሪቱ ፕሬዝዳንት ያልተስማማበትን የሕግ ረቂቅ ለፓርላማ የመመለስና እንደገና ውይይት እንዲደረግበት የማድረግ መብት ይኖረዋል፡፡ ፕሬዝደንቱ እንደገና እንዲታይ የመለሰው የሕግ ረቂቅ በተወካዮች ምክር ቤትና በፌደሬሽን ምክር ቤት የጋራ ስብሰባ በሦስት አራተኛ ድምጽ ከተደገፈ ፕሬዝደንቱ ባይስማማበትም ሕግ ሆኖ ይወጣል፡፡

1.3.1.6. በአስፈጻሚ አካል ውስጥ በፖለቲካ ሹመት የሚመደቡ ኃላፊነቶች ተለይተው እንዲወሰኑ ይደረጋል፡፡ ማንኛውም የፌዴራል መንግስት የፖለቲካ ሹመትና ሥልጣንና ኃላፊነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብቻ የሚወሰኑ ይሆናሉ፡ ፡ ሹመቱን የማጽደቁ ስራ የእያንዳንዱ እጩ ብቃት በነጠላ በመመርመር ይከናወናል፡፡

1.3.1.7. በአስፈፃሚው አካል ሥር የሚዋቀረው ሲቪል ሰርቪስ ከፖለቲካ ገለልተኛ በሆነ መንገድ በችሎታ እና ብቃት ላይ ተመስርቶ በግልጽነትና በተጠያቂነት መንፈስ የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት በሚችልበት ሁኔታ ይደራጃል፡፡

1.3.1.8. ዜጎች የየአካባቢያቸውን የፍትህና የፖሊስ ሃላፊዎች በዴሞክራሲያዊ መንገድ እንዲሾሙና እንዲሽሩ ተሳትፎ የሚያድርጉበት ሥርዓት ይዘረጋል፣

1.4. ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች

ፓርቲያችን በሕገ-መንግስት እውቅና የተሰጣቸውን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ አገራችን የፈረመቻቸውን የሰው ልጆችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚደነግጉ ስምምነቶችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የአገራችንን ልዩ ሁኔታ ባገናዘበ የቡድን (የብሔረሰብ፣ የሀይማኖት፣ ወዘተ) መብቶች ከግለሰብ መብቶች ጋር ግጭት በማይፈጥረበት መልኩ ጥበቃ የሚደረግለት ሲሆን፤ በጥናት ላይ የተመሰረተ የቡድን ፍላጎት ለማደበር እንዲችሉ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ የሚዲያ ተቋማት እንዲሁም ሲቪል ማህበራት የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ለማዳበር በነፃነት እንዲደራጁ አስፈላጊው ድጋፍ የሚደረግ ይሆናል፡፡

DRAFT

1.5. የሃገር መከላከያ ሰራዊት፣ ፖሊስና ድህንነትን

1.5.1. የሃገሪቱ የፀጥታና ደህንነት ተቋማት በሙሉ፤ የሃገሩቱን ሕገ-መንግሥት ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ ለህግ የበላይነትና ለዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር በጽናት የሚቆሙ ከፍተኛ እውቀትና ብቃት ባላቸው መሪዎችና አባላት የተደራጁ ተደርገው ይገነባሉ፤

1.5.2. የአገራችን የመከላከያ፣ የደህንነት እና የፖሊስ ተቋማት የአገሪቱን ዜጎች እና ሉዓላዊነት ከማንኛውም ስጋቶች ሽብርተኝነትን ጨምሮ ለመጠበቅ እንዲችሉ፤ የአከባቢያችን ጂኦ ፖለቲካዊ ሁኔታዎች እና የአገሪቱን አቅም ባገናዘበ መልኩ ሙያዊ ጥራቱና ወቅታዊነቱ የተረጋገጠ ሥልጠና እና ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

1.5.3. የመከላከያ፣ የደህንነት እና የፖሊስ ተቋማት መንግስት በተቀያየረ ቁጥር የማይቀያየሩ እንደተቋም ቋሚ ሆኖ የመቀጠል ዋስትና ይኖራቸው ዘንድ ከማንኛውም ፖለቲካዊ ፓርቲ ወገንተኝነት የራቁ ተቋማት እንዲሆኑ ይደረጋል፤

1.5.4. የመከላከያና የፖሊስ አባላት ከመደበኛ ወታደራዊ/ፖሊስ ሙያ ውጭ በተለያዩ ሙያዎች የሰለጠኑ፣ ግዳጆች በሌሉባቸው ሰላማዊ ወቅቶች፣ ህዝብን በጤና፣ በደን ልማት፣ በሌሎች ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ አገልግሎት፣ በአደጋ ደራሽነት ስራዎች ለማገልገል የሚያስችለው ብቃት ያለው ተቋም ተደርጎ ይደራጃል፣

1.5.5. የመከላከያ፣ የፖሊስና ደህንነት ተቋማት ለሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች፣ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ ባህል ተላባሾች የእምነት ባለቤቶች ተሳታፊነትን የሚያበረታታና የሚያደፋፍር ፖሊሲዎች ያለውና ፖሊሲዎቹን በተግባር የሚተገብር እውነተኛ ሃገራዊ ተቋም እንዲሆን ይደረጋል፣

ቦርድ የተደረጉ ሃሳቦች

- **ኢይዲዮሎጂያችንን ምን ተብሎ ይገለፅ (ሊብራል፣ ሶሻል ዲሞክራት፣ ወይስ ምን? ....)**
- **የሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ (አራንጓዴ ቢጫ ቀይ ተብሎ ቢገለፅ)**
- **አማርኛ ብሔራዊ ቋንቋ ተብሎ ይገለፅ**

አዲስ አበባ የፌዴራል መሆኗን ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

2. የኢኮኖሚ ፕሮግራም

ፓርቲያችን ከሚከተለው የፖለቲካ ፍልስፍና/ማህበራዊ ፍትህ/ ጋር የሚጣጣም ለዜጎች ኤኮኖሚያዊ ነፃነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ የኤኮኖሚ ፕሮግራም እና ፖሊሲዎችን ይቀርፃል፡፡ ፓርቲያችን የመንግስት የኤኮኖሚ ጣልቃገብነት ሊኖር የሚችልባቸውን ዘርፎች በመለየት በግልፅ የሚስቀምጥ ሲሆን በማንኛውም ሁኔታ ከዜጎች ጋር መንግስት ውድድር ውስጥ ሊገባ የሚችልበት እድል አይኖርም፡፡

2.1. *መርሆዎች*

2.1.1. ፓርቲያችን ለዘላቂ ልማትና ብልጽግና ትኩረት በመስጠት የሕብረተሰቡን አጠቃላይ የኑሮ ደረጃና ማሕበራዊ ሕይወት የሚያሻሽል ገበያ መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ይከተላል፡፡ የግሉ ክፍለ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዋና አንቀሳቃሽ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ይሁን እንጂ ከፍተኛ የሥራ አጥነት ሲከሰት፣ የኢኮኖሚ መቆርቆዝ ሲያጋጥም፣ የዋጋ ግሽበት ሲመጣ፣ የመንግስት የበጀት ጉድለት ሲጨምር እና መሰል ችግሮች ሲከሰቱ መንግስት በእውቀትና በጥናት የተመሰረተ ጊዜያዊ የማረጋጋት እርምጃ ይወስዳል፡፡

2.1.2. ከፍተኛ ካፒታል የሚጠይቅ፣ አዋጪነቱ አጠያያቂ ወይም የሚያስገኘው ጥቅም ከረዥም ጊዜ በኋላ ሲሆን ወይም ተፈላጊነቱ ስትራተጂካዊ በመሆኑ እና በመሳሰሉት ምክንያቶች መንግስት ከግሉ ዘርፍ ጋር በሽርክና ወይም

ለብቻው መሰረተ ልማትን ይገነባል፤ የልማት ድርጅቶችን አቋቁሞ ያስተዳድራል፡፡ በግል ባለሀብቶች ሊመሩ የሚችሉ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወደ ግሉ ይዞታ ወይም አስተዳደር እንዲዛወሩ አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል፡፡

2.1.3. ፓርቲያችን ለኤኮኖሚ ዘላቂ ልማት ወሳኝ በሆኑ የመሬትና የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም የነፃ ገበያ ኤኮኖሚን እና የሀገር ሉዓላዊነትን ባስጠበቀ መልኩ እንዲከናወን ዝርዝር ፖሊሲዎች ያውጣል፡፡

2.2. *የግብርና፣ የአርብቶ አደርና ዓሣ ልማት*

2.2.1. ግብርና በተመለከተ- አብዛኛው የሀገሪቱ ህዝብ ገበሬ በመሆኑና ግብርናም መተዳደሪያው በመሆኑ፣ ከግብርና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የግብርናውን የኢኮኖሚ ዘርፍ የሚያሳድጉና የገበሬውን ጥቅም የሚያስጠብቁ፣ ከመሬት ባለቤትነት፣ ከግብር፣ ተውፊታዊና ዘመናዊ አስተራረስና ምርት የማሳደግ፣ ከምርት ማከማቸት፣ ከገበያ አቅርቦት፣ ከመሰረተ ልማት እድገት፣ ከአካባቢ ጥበቃ፣ ከምርቶች የአይነት ብዝሃነት ከአምራቹና ከሃገራዊ የምግብ ዋስትና መረጋገጥ፣ ከግብርና ኢንዱስትሪ፣ ከንግድ፣ ከፋይናንስ፣ ከግል ካፒታል ተሳትፎና እድገት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ፖሊሲዎች በማጥናት ተግባራዊ ያደርጋል፣

2.2.2. ሰፋፊ እርሻዎች እንዲስፋፉ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ሲሆን፣ በኩታ ገጠም ያሉ በአነስተኛ ማሣ ላይ ያሉ አርሶ አደሮች በትብብር እንዲያለሙ ማበረታቻ ይሰጣቸዋል፡፡

2.2.3. የእንስሳና የአሳ ሃብትን በተመለከተ- ከግብርና ቀጥሎ የሃገሪቱ አብዛኛው አምራች ሃይል የተሰማራው በከብት እርባታ ላይ ነው። አሳ የሚያሰግሩ ቁጥራቸው ትንሽ ቢሆንም በሃገራችን በቀላሉ ለበርካታዎች የስራ መስክና የከፍተኛ ሃገራዊ ሃብት ምንጭ መሆን የሚችል ነው። ከነዚህ የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የአርብቶ አደሩንና የዓሣ የአስጋሪውን ጥቅም የሚያስጠብቁ ከመሬት፣ ከሃይቆችና ከወንዞች አጠቃቀም፣ ከተውፊታዊና ዘመናዊ ምርት የማሳደግ፣ ምርት አሰባሰብ፣ ከገበያ አቅርቦት፣ ከመሰረተ ልማት እድገት፣ ከአካባቢ ጥበቃ፣ ከምርቶች የአይነት ብዝሃንነትና ጥራት፣ ከአምራቹና ከሃገራዊ የምግብ ዋስትና መረጋገጥ፣ ከግብርና ኢንዱስትሪ፣ ከንግድና ከፋይናንስ እድገት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ፖሊሲዎች በማጥናት ተግባራዊ ያደርጋል፣

2.3. *ኢንዱስትሪ/የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ*

2.3.1. የኢንዱስትሪ/ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አሁን በአገሪቱ ያለውን ከፍተኛ የወጣት ሀይል ወደ ሥራ ለማስማራት የሚችል መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብቶች በዚህ ረገድ ለሚያደርጉት ተሣትፎ ከፍተኛ ድጋፍ የሚያደርግ ፖሊሲ ይነድፋል

2.3.2. ሰፊ የአምራች መሰረት ያለው፣ በአነስተኛና በመሃከለኛ ደረጃ በሚገኙ ኢንዱስትሪዎች አማካይነት ሃገራዊና ከባቢያዊ እንዲሁም አለማቀፋዊ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች በጥራት የሚያመርት፣ ቀጣይነት ያለው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚደገፍ፣ ለጥናትና ምርምር፣ ለፈጠራና ለግኝት በቂ ካፒታል የሚያውል፣ በአከባቢያዊና በአለማቀፍ መድረኮች በምርት አይነትና ጥራት ተፎካካሪ መሆን የሚችል፣ ከገበሬውና ከግብርናው ዘርፍ ጋር በቅጡ የተሳሰረ፣ የአካባቢ ጥበቃን፣ የሰራተኛውን ጥቅምና ደህንነት የሚያስከብር፣ለውጭ ባላሃብቶች ከሃገሬው ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩበትን አግባብ የሚያበረታታ፣ ለሃገራዊ ባላሃብቶች እንክብካቤ የሚያደርግ በጥናት ላይ የተመሰረተ የማንፋክቸሪንግ ፖሊሲ ቀርጾ ተግባራዊ ያደርጋል።

2.4. *የአገልግሎት*

2.4.1. የቱሪዝምና የሆቴል እንዱስትሪውን ጨምሮ ሌሎችንም በሃገራችን ያሉ የአግለግሎት ዘርፎችን በአንድ ስንደምራቸው በርካታ ባለሃብቶች ከከፍተኛ እስከዝቅተኛ ደረጃ የሚሳተፉባቸውና የበርካታ የሃገሪቱ ዜጎች የስራ ምንጭ ናቸው። በአገልግሎት ዘርፉ የተሰማሩት ስራተኞች ቁጥር ከፋብሪካ ሰራተኞች ቁጥር እጅግ ይልቃል። በዘርፉ ጥራትና ልቀት ላይ የተመሰረቱ ለደንበኞቻቸው አስተማማኝ አግለግሎቶች የሚያቀርቡ ድርጅቶች እንዲስፋፉ ማድረግ፣

2.4.2. ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ልዩ ቦታ እንዲኖራት የሚያስችል፣ አገሪቱ ያላትን ቅርሶች፣ ተፈጥሮ በተገቢው በማስተዋወቅ፣ እንዲሁም በኮንፈረንስ ቱሪዝም ልታገኝ የምትችለውን ጥቅም ባገናዘበ መልኩ ባለሀብቶች ተሳትፎ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ የሚፈጠር ሲሆን ትምህርት ቤቶች ለቱሪዝም ሴክተሩ በተጠና ሁኔታ የሰው ሀይል እንዲቀርቡ ፖሊሲዎች ይቀረፃሉ፡፡

2.4.3. የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎች ተለይተው በቂ የመሰረተ ልማትና ምቹ መስተንግዶ እንዲኖራቸው በማድረግ የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ ለማራዘም የተቀናጀ ስራ ይሰራል፡፡

DRAFT

2.5. *የተፈጥሮ ሀብትና መሬት*

በኢትዮጵያ የግዛት ክልል የሚገኝ ማንኛውም የተፈጥሮ ሀብት የሁሉም ዜጎች የጋራ ሀብት ሲሆን፣ አሁን ያለው የመሬት ፖሊሲ ለኢኮኖሚ እድገት ያለውን እንቅፋት በመረዳት የተለያዩ ዓይነት የመሬት አጠቃቀም እና ይዞታ እንዲኖር ያደርጋል፡ ፡ የመሬት ይዞታም በመንግስት፣ በማሕበረሰብ ወይም በግል ሊሆን ይችላል፡፡

2.5.1. በኢትዮጵያ ግዛት ክልል ዜጎች ያልሰፈሩበትን ቦታ ጨምሮ ሌሎች ፓርኮችና ለመንግሥት አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ቦታዎች በመንግሥት ይዞታነት ሊያዙ ይችላሉ፤ በመንግሥት ይዞታነት ያሉ ቦታዎች ግልፅ በሆነ መሰፈርት እና የገበያ ዋጋ ወደ ግል ሊዛወሩ ይችላሉ፤

2.5.2. በአርብቶ አደር አካባቢ ለግጦሽ፣ በሌሎች አካባቢም ለልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎት የሚውሉ በማሕበረሰቡ የሚተዳደሩ የወል የመሬት ይዞታዎች ሊኖሩ ይችላሉ፤

2.5.3. ዜጎች መሬትን በግል ይዞታነት በባለቤትነት መያዝ፣ ማከራየት፣ መግዛት መሸጥና መለወጥ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

2.5.4. ፓርቲያችን የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት ግልፅ የሆነ የአረንጓዴ ልማት ፖሊሲ ቀርፆ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

2.6. *የከተማ ልማት*

2.6.1. ፓርቲያችን አሁን አገራችን የምትገኝበትን ዝቅተኛ የከተሜነት ደረጃ ለመለወጥ፣ ቢያንስ በአፍሪካ ደረጃ በአጭር ጊዜ ለመድረስ የሚያስችል የከተሞች መስፋፋትን ያበረታታል፡፡ ክልሎች በተቻለ ሁኔታ ከአንድ ርዕሰ ከተማ ውጭ ለመፍጠር እንዲችሉ ማበረታቻ ይደረጋል፡፡ ዜጎች በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ተዘዋውረው መስራት የሚችሉበትን ሰላማዊ ሁኔታ በመፍጠር የተለያዩ ከተሞች እንዲፈጠሩ የሚያበረታታ ፖሊሲ ይቀረፃል፡፡

2.6.2. የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ከተሞችን ለመመስረት በሚያመች መልኩ እንዲሆኑ በማድረግ በገጠር መሬት ላይ ያለውን ጫና በመቀነስ ምርታማነት እንዲያድግ እገዛ የሚያደርግ ከተሜነት ያበረታታል፡፡

2.6.3. ከተሞች የአረንጓዴ ልማትን ያካተቱ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊነት

2.7. ***መሰረተ ልማትን***

2.7.1. መሰረተ ልማት ባጠቃላይ ኢኮኖሚውን አሳላጭና የሚያሳድግ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የስራ ፈጣሪ የኢኮኖሚ መስክ ነው። ማንኛውም የመሰረተ ልማት ስራ በሃገር ውስጥ ባለሃብቶችና ባለሙያተኞች፣ በሃገር ውስጥ ሰራተኞች በሃገር ወስጥ በሚመረቱ የእቃ አቅርቦቶች የሚሰራበትን አግባብ ማመቻቸት፣ አቅም መገንባት ማናቸውንም የተለያዩ አሰፈላጊ ድጋፎች በማድረግ በከፍተኛ ጥራትና ልቀት የሚፈጽም ይሆናል። የተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች ተመጣጣኝ የሆነ የመሰረተ ልማት ሽፋን እንዲያገኙ፣ በመሰረተልማት መረብ እንዲተሳሰሩ የሚያደርግበጥናት ላይ የተመሰረተ የመሰረተ ልማት ፖሊሲ ተግባራዊ ያደርጋል።

2.7.2. ትራንስፖርት፣ ኮምኒኬሽን፣ የዉሃና ፍሳሽና የኤሌክትሪክ አገልግሎቶች ከህዝቡ ገቢ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ በብዙሃን ማጓጓዣ ላይ የተመሰረተ የባቡሮችና የአውቶቡሶች አገልግሎቶች ማስፋፋት፣ ከኤሌትሪክ ማመንጨት እድገት ጋር ተያይዞ የሃገሪቱን የተለያዩ ክልሎችና ከተሞች በኤሌትሪክ ጉልበት በሚሰሩ ከተማና ክልል አቋራጭ የባቡር መጓጓዣዎች ማስተሳስር፤ አካባቢንና አየርን የሚበክሉ ማናቸውንም አይነት የመጓጓዣ ዘዴዎችን የሚቀንስ የትራንስፖርት ፖሊሲ መከተል፣

2.8. *የፋይናንስ እና የባንክ የአገልግሎት*

19.1. ጥብቅ የሆነ የፊስካል እና ሞኒታሪ ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ፣ ከአቅም በላይ መንጠራራትን፣ ከሃገሪቱ አመታዊ ገቢ የመከፈል አቅም ጋር ሲነጻጸር አደገኛ የሆነ፣ከውጭ ሃገርም ሆነ ከሃገር ውስጥ በመንግስት የሚወሰድን የብድር ስርአት የማይፈቅድ፣ የዋጋ ግሽበትን የሚቆጣጠር፣ የህዝብ ንብረት ብክነትን ለመቆጣጠር የሚያስችል የአካውንቲንና የኡዲቲንግ ሙያተኞችን ሃላፊነትን ያገናዘበ ህጋዊ ጥበቃ የሚደረግለት ነፃና ገለልተኛ የተመሰረተ የፋይናንስና የባንክ ፖሊሲ ተግባራዊ ያደርጋል፣

19.2. በጥናት ላይ ተመስረቶ ተገቢውን ወለድ በመክፈል የገንዘብ ቁጠባን የሚያበረታታ፣ የቢዝነስ የንግድና የፕሮጀክቶችን አዋጭነት በመገምገም ያለ ማስያዣ ለታታሪ ሰራተኞች ብድር የሚያሰጥ አሰራርን የሚያበረታታ፣ ባንኮች ከወለድ ነፃ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የፋይናንስ ሴክተር በዘር፣ በሀይማኖት ተለይቶ እንዳይደራጅ ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

3. የማሕበራዊ ፕሮግራም

የፓርቲያችን ማህበራዊ ፕሮግራመ መሠረቱ በተለያየ የተበላሻ የመንግሥት ፖሊስ በመገፋት ከኤኮኖሚ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ እንዲርቁ የተደረጉ ብቻ ሳይሆን በዚሁ መነሻ በከፍተኛ ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን በስርዓት ውስጥ ለማካተት የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት ነው፡፡ ዜጎች በማህበራዊ ዘርፍ ፓርቲያችን የሚወስዳቸውን ተጨባጭ እርምጃ በመጠቀም እራሳቸውን ጠቅመው ለአገር የሚተርፉ ዜጎች ማድረግ የማህበራዊ ፕሮግራማችን ቀዳሚ ትኩረት ነው፡፡ የፓርቲያችን ፕሮግራም በምንም መልኩ ሥራ ጠልነት እና ድጋፍ ጠባቂነትን አያበረታታም፣ ዝርዝር ፖሊሲዎችም ይህን መሠረት ያደረጉ ይሆናሉ፡፡

3.1. ድህነት ማጥፋት

ድህነት የመንግሰት ፖሊስ ውጤት ከመሆኑ በተጨማሪ ዜጎች ድህነትን በመጠየፍ የሚወስዱት ተነሳሽነት እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ ዜጎች ለስራ ያላቸውን ተነሳሽነት የሚያነሰብቱ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስራዎች ይስራሉ፡፡

3.2. የሰው ሀይል ፍልሰትና ስደት

ዜጎች ሀገራቸውን ለቀው ለስደት የሚነሳሱት በሀገር ውስጥ በሚኖር የኤኮኖሚ አማራጭ እጦት፤የገዢው ፓርቲ ለደጋፊዎቹ በሚያደርገው አድሎአዊ አስራር እንዲሁም በነፃነት ተዘዋውሮ ለመስራት በተለያየ መንገድ በሚደረጉ ፖለቲካዊ ገደቦች ናቸው፡፡ ዜጎች በአማራጭ የሰራ ፍላጋ ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ጋር ተወዳድረው መሰራታቸው ችግር እንዳልሆነ ሁሉ፤ በዝቅተኛ ስራ ለመሰማራት ሀገር ለቆ ፍልሰትና ሰደት የሚያስቆጭ እውነት ነው፡፡ ይህ እንዳይሆን ዝርዝር ፖሊሲዎች ተቀርፀው ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ ዜጎች የፖለቲካ አመለካከታቸውን መሠረት በማድረግ ከአምራችነት የሚገለሉበት ስርዓት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በሁሉም መስክ ተገቢውን ተሣትፎ የሚያደርጉበት ሥርዓት ይበጃል፡፡

3.3. ትመህርት

3.3.1. ትምህርት ለአገር እድገት ወሳኝ ግብዓት መሆኑን ፓርቲያችን ይገነዘባል፡፡ ተተኪው ትውልድ በእውቀት ላይ መሰረት ያደረገ ዓለም አቀፋዊ ተወዳደሪነት እንዲኖረው የመንግሰት ድጋፍ ያስፈልጋል ብሎ ያምናል፡፡ የትምህርት ፖሊሲያችን ሁሉም ልጆች የመማር መብት እና ወላጆች የማስተማር ግዴታ እንዳለባቸው ከግንዛቤ የሚወስድ ነው፡፡ ዜጎች የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ያለምንም ኤኮኖሚያዊ ጫና ይልቁንም በሚያገኙት ዕውቀት ለሀገር የሚጨምሩትን እሴት ከግምት በማስገባት ይቀረፃል፡፡ የትምህርት ጥራት በማንኛውም ሁኔታ ለድርድር አይቀርብም፡፡

3.3.2. መደበኛ ያልሆኑ የጎልማሶች ትምህርትን በማስፋፋት ትምህርት ሳያገኙ ያለፋቸው ዜጎች በኑሯቸው ስኬታማ እንዲሆኑ፤ ምርታማነታቸው እንዲጨምር ልዩ ፕሮግራሞች ይዘረጋሉ

3.3.3. ቅደመ መደበኛ ትምህርት/መዋለ ሕፃናት ጨምሮ በሁሉም አገሪቱ ክፍል እንዲስፋፋ ዝርዝር ፖሊሲዎች ይዘጋጃሉ፤

3.3.4. የትምህርት ጥራትን ለማሰጠበቅ እንዲቻል በየደረጃው በመንግሥት በነፃ ከሚሰጥ ትምህርት በተጨማሪ አቅምን ያገናዘበ የወጪ መጋራት ተግባራዊ ይሆናል፤ ተመራቂዎች ወጪያቸውን ከምረቃ በኋላ በሚሰጡት ማህበራዊ አገልግሎት የሚሸፈንበት ሥርዓት ይበጃል፤

3.3.5. ለትምህርት ጥራት መጠበቅ የመምህራን ጉዳይ ወሳኝ በመሆኑ፤ የመምህራንን የአስተማሪነት ክብር በችሎታቸው፣ በስነምግባራቸው፣ በስልጠና እና በተሻለ ኑሯቸው እንዲታደስ በማድረግ በተማሪዎቻቸው ላይ ማሳደር የሚችሉትን በጎ ተጽእኖ ማሳደግና ሌሎችንም ነጥቦች ያካተተ ዝርዝር ፖሊሲ በማውጣት ተግባራዊ ያደርጋል።

3.3.6. የትምህርት ጥራትን በጠበቀ ሁኔታ የግል ባለሀብቶች በትምህርት ዘርፍ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የፖሊሲ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

3.4. የጤና አገልግሎት

3.4.1. ጤናው የተጠበቀ ዜጋ ለልማት የሚያደርገው አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት፤ ዜጎች በሁሉም ደረጃ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እናቶችና ሕፃናት የሚፈልጉትን የጤና ክብካቤ ሁሉ በአካባቢያቸው እንዲያገኙ ግድ ነው፡፡ ወጪ ቆጣቢ ተደራሽ የጤና አገልግሎት ለሁሉም ዜጋ ለማዳረስ መንግሥት ኃላፊነቱን መወጣት አለበት በሚል መሰረት ዝርዝር የጤና ፖሊሲዎችን ያወጣል፡፡ ወጪ መጋራት ለአገልግሎት ጥራት ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ ዝርዝር ሁሉአቀፍ የጤና አገልግሎት የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን ይፋ ያደርጋል፡፡

3.4.2. ቅኝቱ በሽታ አስቀድሞ በመከላከል ላይ የተመሰረተ ለብዙሃኑ የገጠርና የከተማ ኗሪ ተደራሽ የሚሆን የጤና ራእይ ይሆናል፡፡ ከመከላከል ቀጥሎ ዜጎች በቀላሉና በርካሽ መድሃኒት ለሚገኝላቸው በሽታዎች በየቤታቸውና

DRAFT

በየቀበሌያቸው ሲሰቃዩ ውለው የሚያድሩበትን የስቃይ ዘመን የሚያስቆም ለበሽተኞች በፍጥነት መድረስ የሚችል የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና እርዳታ ማስፋፋት፣

3.4.3. የጤና አገልግሎቶት ለማስፋፋት እና ለሁሉም ተዳራሽ እንዲሆን ለማድረግ በሚደረገው ጥረት የግል ባለሀብቶች ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጡ አስፈላጊው የፖሊሲ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

3.5. ማህበራዊ ዋስትና

የማህበራዊ ዋስትና ለዜጎች መሰጠት ለአንድ ሀገር ግዴታ መሆኑን በመረዳት፤ ዜጎች ይህን ለማድረግ የሚያስችል ተመጣጣኝ መዋጮ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡ በፍላጎታቸው በሚያደርጉት መወጮ መሰረትም መብታቸው ሊከበርላቸው የሚችልበት ስርዓት ይዘረጋል፡፡ ማህበራዊ ዋስትና የሚያስፈልጋቸውን ዜጎች ከኤኮኖሚ እድገት ደረጃ ጋር እየተገናዘበ ማስተካከያና ማሻሻያ ይደረግበታል፡፡ አሁን በስራ ላይ ያለው በማህበራዊ ዋስትና ስም የግል ተቀጣሪ ሰራተኞች ገንዘብ እንዲያዋጡ፤ ነገር ግን በምንም መልኩ ተጠቃሚ የማይሆኑበት ስርዓት ይለውጣል፡፡ ዜጎች ሁሉ ወጥ የሆነ የማህበራዊ ዋስትና መለያ እንዲኖራቸው በማድረግ ተጠያቂነት ያለው የማህበራዊ ዋስትና ስርዓት ይዘረጋል፡፡

3.6. ሴቶች

ፓርቲያችን ሴቶችን ያገለለ ማንኛውም ዓይነት ፖሊስ ውጤታማ እንደማይሆን ይገነዘባል፡፡ በተለይ የሴቶች በፖለቲካው መስክ መሳተፍ የራሳቸውን ጉዳይ በጥልቅ ያገናዘበ ፖሊስ ለመቅረፅ ፋይዳው የጎላ እንደሚሆን ያምናል፡፡ ትምህርት ለእኩል ተሣትፎ ወሣኝ መሣሪያ በመሆኑ ሴት ልጆች ከትምህርት ገበታ የሚያስቀሩ ማነቆዎችን በማስወገድ ዘላቂ የሆነ የሴቶች ተሳትፎን ለማረጋገጥ ይሰራል፡፡ ሴቶች አሁን ያለው የፖለቲካ ምዕዳር የፈጠረው አፈና ሲነሣ ሙሉ ሀይላቸውን ሊጠቀሙ የሚችሉበት ዕድል እንደሚፈጠር ፓርቲያችን ያምናል፡፡ ለይስሙላ ለፖለቲካ ፍጆታ በሚል የሚደረጉ የሴቶችን ተሳትፎን ፓርቲያችን አይቀበልም፡፡

3.7. ወጣቶች

በሀገራችን የሚታየው የወጣት ስራ አጥነት በግልፅ የሚያመለክተው፤ አገሪቱ ያላትን ወሣኝ የእድገት ምንጭ በአግባቡ መጠቀም ያለመቻሏን ነው፡፡ ይህን እምቅ የእድገት ምንጭ የሆነውን የወጣት ሀይል አሟጦ ለመጠቀም እንዲቻል፤ ይልቁንም ወጣቱን ከወላጆቹ ጋር በተጣበበ የግብርና መሬት ላይ የሚያደርገውን የመሬት ቅርምት በማላቀቅ ከግብርና ውጭ ባሉ የስራ እድሎች ተሣታፊ ለማድረግ የተቀናጀ የከተማ ልማት ስትራቴጂዎች ይቀረፃሉ፡፡

3.8. አካል ጉዳተኞች

በአሀገራችን ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነ የተለያየ የአካል ጉዳት ያላባቸው ፤ነገር ግን በአገር ዕድገት ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ ማድረግ የሚችሉ ዜጎች ይኖራሉ፡፡ አካል ጉዳተኞችን ከግምት ውስጥ ያስገባ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ያለመኖር፣ አድሎዋዊ የስራ ቅጥርና ምደባ፣አስፈላጊው የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች አለመኖር፣ ወዘተ፣ ኑሮዋቸውን አስቸጋሪ ያደረገው መሆኑን ፓርቲያችን ይገነዘባል፡፡ ይህን አስቸጋሪ ሁኔታ ለመለወጥ የሚያስችል ዝርዝር ፖሊሲ ወጥቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

3.9. አረጋውያንና ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት

ተንከባካቢ የሌላቸው አረጋዊያን እንዲሁም ወላጅ ያጡ ህፃናትን መንከባከብ ለበጎ ምግባር በሚዘጋጁ ዜጎች ብቻ የሚተው ባለመሆኑ አስፈላጊው ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያገኙ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ህፃናትን ለልማና ተግባር ማዋል እንዲቀር የሚያደርግ ፖሊሲ ተቀርፆ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

3.10. ስነ ሕዝብን

የተመጣጠነ የህዝብ እድገት ለዘላቂ ልማት ወሣኝ መሆኑን በመገንዘብ ሀገሪቱ የምታስመዘግበውን እድገት በማይፃረር መልኩ፤ የስነ ህዝብ ፖሊሲ ተቀርፆ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የህዝብ ቆጣራ ውጤቶች ከምንም ዓይነት የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነፃ በሆነ መንገድ እንዲከናወን እና ውጤቱም ለሰብዓዊ ልማት ብቻ የሚውል ይሆናል፡፡

DRAFT

3.11. ቅርሶችና ብሄራዊ ፓርኮች

ፓርቲያችን አገራችን ኢትዮጵያ ያሏትን የቱሪስት እምቅ ሀብት ለመጠቀም እና የዓለም ዋነኛ የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ የሚያስችል ዝርዝር ፖሊሲዎችን ይቀርፃል፡፡ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ የፓርኮች ልማት ይካሄዳል፡፡ ለቅርሶች የሚደረገው ጥበቃ ዘመናዊ እንዲሆን የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፡፡

3.12. ስፖርት፣ ኪነጥበብ፣ አርት ሳይንስና ቴክኖሎጂ

ፓርቲያችን ኪነጥበብ አርት፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም ስፖርት እንዲስፋፉ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡

በዚህ ፕሮግም ስር የተጠቀሱትን አጠቃላይ መንፈስ መሰረት ያደረገ ዝርዝር ፖሊሲ በሁለም ዘርፎች ይዘጋጃሉ፡፡ ህዝቡም እንዲያውቀው በተለያዩ መድረኮች እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡ በፓርቲያችን ዌብ ሳይት እና ሌሎች መንገዶች ህዝቡ እንዲያገኘው ይደረጋል፡፡

4. የውጭ ግንኙነትና የአከባቢ ሰላም ፕሮግራም

ፓርቲያችን የኢትዮጵያ መሰረታዊ የደህንነትና የጥቅም አደጋዎች የሚመነጩት ከውጭ ይልቅ በውስጥ በተሸከምናቸው በሁሉም ዘርፎች ከሚታዩ ችግሮቿ ጋር የተሳሰሩ መሆናቸውን የተረዳ፣ እነዚህ ችግሮች በአለም አቀፍ መድረክ መጫወት ይገባት የነበረውን ትልቅ ሚና ያቀጨጩት መሆኑን የተገነዘበ፣ እነዚህን ችግሮቻችን በማባባስ ትልቅ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችሉ የጎረቤት ሃገሮች እንዳሉን የሚያውቅ፣ ከምንም በላይ ቅድሚያ ለኢትዮጵያ እና ለዜጎቿ ጥቅሞች የሰጠ፣ ኢትዮጵያ በፖለቲካ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ዘርፎች ለገጠሟት ውስብስ ችግሮችና ለምትገኝበት አሳሳቢ ሁኔታ መፍትሄ በመስጠት እገዛ ማድረግ የሚችልና በሂደትም ሃገሪቱ በአካባቢዋ ይሁን በአፍሪካ ከዛም አልፎ በአለም መድረኮች ተደማጭነት የሚያሰጣት፣ በሂደትም ከፍተኛ የእድገትና የስልጣኔ ማማ ላይ እንድትቀመጥ የሚረዳ፤ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ይኖረናል። በዚህ መነሻ፤

4.1. አጠቃላይ

4.1.1. በከፍተኛጥንቃቄና ጥናት ላይ በመመስረት ሃገራችን ጥቅሟንና ደህንነቷን የበለጠ ማስከበር ያስችላሉ ብላ ከምታምናቸው የአለም ሃገራት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ትመሰርታለች፣ በተመሳሳይም መሰረታዊ ጥቅሟን ሊጻረሩ የሚችሉትን በጥናት በመለየት ራሷን በሁሉም መልኩ ለመከላከል የሚያስችል ዝግጅት ታደርጋለች፣

4.1.2. ለሰው ልጆች ሰላም፣ መብት መከበር፣ ብልጽግና፣ የአካባቢ ጥበቃና ሌሎችንም በጎ አስተዋጸኦ ለአለማችን ከሚያበረክቱ ተቋማትና ድርጅቶች ጋር በቅርበት ትሰራለች፣ ተልእኳቸውም እንዲሳካ የምትችለውን ድጋፍ ታደረጋለች፣

4.1.3. መንግስታት በስምምነትያጸደቋቸው አለም አቀፍ ህጎችና ስምምነቶች በሁሉም ሃገራት እንዲፈጸሙ፣ የሃገራችን ሉዓላዊነት እንዳይገሰስ፣ ደካማው በጠንካራው እንዳይጠቃ፣ የተባበሩት መንግስታት ፍትሃዊ የውሳኔ መስጫ አግባብ እንዲኖረውና እንዲጠናከር፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በሁሉም መስኩ ጎልብቶ ዋንኛው የአፍሪካ ችግር ፈቺ ወሳኝ ሃይል ሆኖ እንዲወጣ የሚያደርግ እንቅስቃሴ በሙሉ ትደግፋለች፣

4.1.4. ማንኛውንም ሃገራችን የፈረመቻቸውን አለምቀፍ ድንጋጌዎችና ህጎች ታከብራለች፣ ጥቅሟን ለማስከበር የምትወስዳቸው ማናቸውም እርምጃዎች በእነዚህ ህጎችና ድንጋጌዎች ማእቀፍ ውስጥ እየተፈጸሙ መሆኑን እያረጋገጠች ተግባራዊ ታደርጋለች፣

4.1.5. የአለምን ሰላምና ደህንነት የሰው ልጆችንና ነጻነት ለመግፈፍ በአለም ላይ ሽብርና ሁካታ ለመፍጠር የሚፈልጉ ሃይሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አለም አቀፍ ማህበረሰቡ በጋራ የሚያደርገውን ጥረት በተቻላት አቅም ትደግፋለች፣

4.1.6. ሀገራችን ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች እና መንግስታት ጋር የምታደርገው ግንኙነት የራሷን ደህንነትና ጥቅም ለማስቀደም ቅድሚያ እየሰጠች በረጅም ጊዜ በጋራ ጥቅም፣ በእኩልነት፣ በመከባበር እና በእርስ በርስ የውስጥ ጉዳዮች ጣልቃ ባለመግባት መርሆች ላይ የተመሰረተ ይሆናል፤

4.2. ጎረቤት ሃገሮችን በተመለከተ

4.2.1. ፓርቲያችን ከጎረቤት አጋራት ጋር የሚኖረን ግንኙነት በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን፣ ከጥርጣሬና ካለላስፈላጊ ውድድር ነፃ ሆኖ በጋራ መልማትና የቀጠናውን ሰላምን ማረጋገጥ ላይ ያተኮረ እንዲሆን ይሰራል፡፡

4.2.2. የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያችን በአካባቢያችን እየተደቀኑብን ያሉትን ስጋቶች በሚገባ የተገነዘበ፤ ከዚሁ አንጻርም የአገራችንን የረጅም ጊዜ ጥቅምን በሚገባ ለማስጠበቅ የሚያስችል ይሆናል፡፡

4.2.3. ከዓለም አቀፍ ሕግጋትና ከታሪክ አንጻር አገራችን ራስዋ ባለቤት ሆና የምታስተዳድረው (sovereign ownership) የባህር በር እና መተላለፍያ (ኮሪዶር) የማግኘት መብት ሊኖረን እንደሚገባ ፓርቲያችን ያምናል፡፡ ከአካባብያችን እና ከሃገራችን ልዩ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ደግሞ ይህን መብት የማስከበር ጉዳይ የኢኮኖሚ እድገት ብቻ ሳይሆን የሃገር ደህንነት እና የሃገር ህልውና ጉዳይ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ይህን በሠላማዊ፣ ህጋዊና እና ዲፕሎማሲያዊ መስመር ተግባራዊ ለማድረግ ይሰራል፡፡

4.2.4. ፓርቲያችን ሀገራችን ያሏትን የተፈጥሮ ሀብቶችን በተለይ ደግሞ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችን የመጠቀም ተፈጥሯዊ መብት እንዳላት ያምናል፤ ይህንንም ከአገሮች ጋር በስምምነት ለመፈፀም እና የትብብር እንጂ የግጭት መንስዔ እንዳይሆኑ አበክሮ ይሰራል፡፡

4.2.5. ከጎረቤት ሃገራት ጋር የሚደረግ ግንኙነት የሚመራው ከሌሎች ሃገሮች ጋር በሚደረጉ መሰረታዊ መርሆዎች ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ ግን የጎረቤት ሃገሮች በራሳቸውም ይሁን የሌሎች ሃይሎች መሳሪያ በመሆን በሃገራችን ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖአሳዳሪ መሆን ስለሚችሉ በሚገባ የታሰበበት በጥናትና ምርምር ላይ የተደገፈ በጥንቃቄ የሚያዝ ፖሊሲ ይቀረጻል፣

4.2.6. ከጎረቤት ሃገሮች ጋር የሚኖር ግንኙነት የየሃገራቱን ማንነትና ምንነት በሚገባ ያጠና፣ በቀላሉ ለጋራ ጥቅም መቆም የሚችሉትን፣ ለጋራ ጥቅም በጋራ ለመስራት የተለያዩ ችግሮች ያለባቸውን ሃገራት በመለየት ለእያንዳዳቸው የሚሆን ስትራተጂ የነደፈ ፖሊስ ተግባራዊ ይደርጋል፤

4.2.7. በአካባቢው መልካም ጉርብትናን በመፍጠርና በማቀራረብ በሁሉም ሃገራት የነበሩ የፖለቲካ ስርአቶች የፈጠሩትን የቁርሾ፣ የመጠራጠር ስሜት በማጥፋት፣ ለመልካም ጉርብትናው ዋስትና መሆን የሚችሉ የፖለቲካ የማህበራዊና የኢኮኖሚ እሴቶች የሚጋሩ በነዚህ እሴቶች ዙሪያ ሃገሮቻቸውንና ህዝቦቻቸውን በሁሉም መንገድ የሚያስተሳሰሩ፣ ከጋራ ኢኮኖሚ ግንባታ እስከ ጋር መከላካያ ለማቆም የሚዘልቅ የጋራ ጥቅም ማስከበሪያ ስትራተጂ ነድፎ እስከ መንቀሳቀስ የሚወስድ ሩቅ አላሚ ፖሊሲ እንዲቀረጽና በስራ ላይ እንዲውል ይደርጋል፣

5. በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን

በተለምዶ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ተብሎ የሚጠራው፣ ከኢትዮጵያ ውጭ በሌላው አለም ተበትኖ የሚኖረው በአንድ ወቅት ምንጩ ኢትዮጵያ የሆነው ሁሉ በዚህ ፕሮግራም ትውለደ ኢትዮጵያ ተብሎ የሚጠራው ነው። ከሃገሩ የወጣበት ምክንያት የፈለገው ይሁን፣ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌላም ይሁን፣ በፈለገው የተለያዩ ማህበረሰቦች፣ ቋንቋን ሃይማኖትን የሙያ ዘርፍ፤ ወዘተ ለይቶ በተከፋፋፈለ ሁኔታ በወጭ ሃገራት እየተሰባሰብ ወይም ተበትኖ ይኑር፣ በአንድ ወቅት ምንጩ ኢትዮጵያ እስከሆነ ድረስ በአገራችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለማድረግ ትልቅ ሀይል ነው ብሎ ፓርቲያችን ያምናል።

የፖለቲካ ፍልስፍናውን ማህበራዊ ፍትህ አድርጎ የሚንቀሳቀስ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ፤ የፓርቲውን ፕሮግራም በሚገባ ለማስፈጸም ዝግጁ የሆነ ፓርቲ በአገር ውስጥ ከተፈጠረ፤ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ትልቅ ድጋፍ ሊሰጥ የሚችሉ በመሆናቸው ተገቢው ትኩረት ሊሰጠቸው እና ግልፅ ፖሊሲ ሊወጣላቸው እንደሚገባ ይታመናል። ፓርቲያችን፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊያንን የሚመለከት ግልፅ ፖሊሲ ሊኖረው የግድ የሚያደርገው በውጭ ያሉት አባላቱና ደጋፊዎቹ የሚመኙትን፤ ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊና የበለጸገች ሃገር ለማድረግ በብዙ ዘርፎች ወሳኝ ሚና መጫወት እንደሚችሉ ሰለሚያውቅ ነው።

ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በአብዛኛው እንደሚታሰበው ተንደላቀው የሚኖሩና በምቾት የቀበጡ አድርጎ መሳል ስህተት ነው፡፡ እጅግ ብዙ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በአስከፊ ሁኔታ በሰው አገር እንደሚኖሩ ይታወቃል፡፡ አብዛኞቹ የሚኖሩት ዴሞክራሲ በዳበረባቸው ሃገሮች ነው። በነዚህ ሃገሮች በመኖር ብቻ ሰብአዊ መብት፣ የሚድያና የግለሰቦች ነጻነት፣ የህግ የበላይነትና የፍትህ ሚዛናዊነትን ለመረዳት፣ በዚህ መንገድ በሰለጠነ ሁኔታ፣ የተረጋጋና የበለጸገ ሃገር ፈጥረው በሚኖሩ ህዝቦች እንዲቀኑ ተደርጓል። “ምነው ኢትዮጵያም እንዲህ የሞላላት ሃገር ብትሆን” ብሎ የማይቀና ትውልደ ኢትዮጵያዊ አባል አይኖረም። ይህ ማለት የተሳትፎው ጉዳይ ቢለያያም በውጭ የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ሃገራችን ነጻነት፣ ፍትህ፣ ዴሞክራሲ የሰፈነበት ሃገር እንድትሆን ያደረጉት ትግልና የከፈሉት መስዋእትነት ወደፊትም የሚኖረው አስተዋጸኦ ቀላል አይሆንም።

ስለዚህ በሚኖሩበት አገራት ያካበቱትን ልምድ፣ እውቀትና ሀብት ከአገራቸው ጋር እንዲያስተሳስሩ፣ ድጋፋችን የሚሹ በችግር ላይ ላሉትም ተስፋ የሚሰጥና የሚደግፍ፤ ሁሉን አቀፍ የሆነ ምቹ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚ እና ማህበራዊ ተሳትፎ ሊያድርጉ የሚችሉበት ፖሊሲ ፓርቲያችን አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ፖሊሲው በሁሉም ደረጃ ግብዓት እንዲያገኝ ጥልቅ ውይይት ይደረግበታል፡፡

DRAFT